# አህያውን ፈርቶ ዳውላውን

ወንድማችን ቴዲ አፍሮ ፍጹም ኢትዮጵያዊነትን አብሮ መኖርን ሰላምን ስላዜመ ወያኔ ለማንም በማያጣራጥር መንገድ ወንጀል አቀናብሮለት እስር ቤት ወረወረው። ተበዳዩን ተጠቂውን ምክንያት ፈልጎ ማንኳሰስ ልምድ ካደረጉ ወይም በዳዩን ላለመናገር መሀላ ካደረጉ ኢትዮጵያዊያን ስለጉዳዩ ሲሰጡ ከነበሩት አስተያየቶች።

"ቴዲ ወያኔን እያወቀ አብዝቶት ነበር።"
"ቴዲ እንደሚጠሉት እያወቀ ማን አገር ቤት ግባ አለው?"
"ቴዲ ዝነኛ መሆኑንን እያወቀ ወንጀል ያለበት አካባቢ ማን ተገኝ አለው?"
"ቴዲ ሲዘፍን የነበረው ለገንዘቡ ነው።"
"ቴዲ ስለኦሮሞ በደል አልዘፈነም" እነዚህንና እነዚህን ይመሳሳሉ አስተያየቶች ናቸው።

በተመሳሳይ ሁኔታ እነመለስ ከምርጫው በኋላ ከህዝብ ፍላጎት ውጪ ስልጣን ላይ ለመቆየት ሲያስቡ የተቃወሟቸውን ዜጎች በቀን ብረሀን ሲጨፈጭፉ ሲያግዙ ምክንያት ፈልገው ተጎጂውን ተበዳዩን ማጥቃት መተቸት ልምድ ካደረጉ አስተያየት ሰጪዎች።

"የወያኔን ባህሪ እያወቁ ማን ተቃወሙ አላቸው፤ ድንጋይ ሲወረውሩ ነበር፤ ድሮስ መለስ በምርጫ ስልጣኑንን ይሰጣል ብለው   ነበር ወይ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ህንጻ መንገድ ተሰርቷል፤ ተቃዋሚዎችስ እንደሚሉት ለውጥ ማምጣታቸውን በምን ይታወቃል ሁሉም ለስልጣን ነው" ይሏችኋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ብዙዎች ፍጹም የሆነ መሰዋትነት ከፍለው ያቆዩልንን አገር ወያኔ እየቆረሰ ሲያድለው፤ "አይ መሬት መሬት እንላለን ያለውን መቼ በአግባቡ አርሰን ጠግበን ኖርንበትና ነው?" ይሏችኋል። ወ/ት ብርትኳንን መለስ ዲሞክራሲ ለመኖሩ ማረጋገጫ እንድትሆን አሰርኳት ሲልና ከናቷና ከአንድ ልጇ ለይቶ ከማንም እንዳትገናኝ አድርጎ አጸያፊ ግፍ ሲፈጽምባት፤ "የመለስን ባህሪ እያወቀች ማን በሽማግሌ በምናምን ተፈታው ብላ ለፍልፊ አላት፤ አርፉ ልጅዋን አታሳድግም፤ ይበላት ማን ወደ አገር ተመለሺ አላት?" ይሏችኋል።

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ በተለያየ ጉዳይ ላይ የተሰጡ አስተያየቶች ብዙ ተመሳሳይነት አላቸው። ሁሉም በፍጹም በዳዩን አጥፊውን ደፍሮ ለመናገር ወኔ ያጡ ናቸው። ሁሉም ተጠቂው ተበዳዩ ላይ ሰበብ ፈልጎ ማጣጣል፤ ተበዳዮች የተፈጸመባቸውን ወንጀል፤ ወያኔዎች በአገርና በህዝብ ላይ የፈጸሙትን ጥፋት ደካማ ወይም የማይገናኝ ምክንያት ሰቶ ትክክል አግባብ ያለው ለማድረግ የሚሞክሩ ናቸው። እነዚህን የመሳሰሉ አስተያየቶች እነመለስን እያወቁ፤ ወያኔን እያወቁ፤ በምርጫ ተሸንፈው ይለቃሉ ብለው ነው ወይ የሚሉ ቃላትን የያዙ ስለሆኑ አስተያየት ሰጪዎች አገርና ህዝብ ላይ የሚፈጸመውን ወንጀል በደንብ የሚያውቁ በፍጹም የእውቀት ችግር የሌለባቸው መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው። እንዚህና መሰል አስተያየቶች በብዛት ፍጹም ወያኔ በአልሆኑ ኢትዮጵያውያን   የሚሰጡ ናቸው። እነዚህና መሰል አስተያየቶች በተለያየ እድሜ እውቀት ጾታ ላይ በአሉ ግለሰቦች የሚሰጡ ናቸው።

ወያኔዎቹ የሚሰጧቸው ምክንያቶች መለስ የመግደልም የማሰርም አገር የመሸጥም መብት አለው ደግ አረክ የሚል እድምታ ያለው ነው፡፡ ወይም መለስ ወይም መንግስት ስለጉዳዩ የሰጠውን ምክንያት ደጋፊዎቹ ህሊና የሚሉት ነገር ስላልፈጠረባቸው በጉዳዩ ሀሳብ ሲሰጡ ጥሬውን እንደሰሙት ነው እንዳለ   የሚያቀርቡት። ንጹሀንን መለስ ጨፈጨፈ ስትሏቸው ደርግም መንግስት እያለ ጨፍጭፏል ኢህአዲግ መንግስት ስለሆነ መጨፍጨፍ ይችላል ወይም መለስ ባንክ ሲዘርፉ ነው ካለ ባንክ ሲዘርፉ ነው የተገደሉት ይሏችኋል። መለስ መሬት ቆርሶ ለሱዳን ሰጠ ካላችኋቸሁ መለስ ስለጉዳዩ የሰጠውን ምክንያት ድሮም ሀይለስላሴም መንግስቱም ሊሰጡ የነበረውን ነው ይሏችኋል። ወያኔዎች ጋር በሙሉ የራስ የሆነ የሚያስብ ጭንቅላት አለመኖሩ የታወቀ ነው። መለስ እንዳለ እንኳ ብንወስደው ሀይለስላሴም መንግስቱም አሰቡ እንጂ አልሰጡም ማሰብና መፈጸም የተለያየ ነገር ነው ለነገሩ አላሰቡምም። ለማንኛውም አነሳሴ ብዙ የተባለባቸው ወያኔ ደጋፊ ነን ባዮቹ ላይ ስላልሆነ እተወዋለው፡፡ የዚህ አይነቶቹ በአሁኑ ጌዜ የሉም ለመባል የሚያስችል ሁኔታ ላይ ነው ያሉት።

ተበዳዩን ማጥቃት ልምድ ያደረጉ ዜጎቻችንን ለምን እንደዚህ ያስባሉ፤ ለምን ቀላሏን ሀላፊነት የሌለባትን መንገድ መረጡ ብለን ማሰባችን አይቀርም። የዚህ አይነት ሰዎች ቤተሰቦቻችን ውስጥ ጓደኞቻችን መሀል በብዛት

የምንገናኛቸው ናቸው። እራስ ምታት እንደለቀቁብን እንደተጨቃጨቅናቸው እንኖር ዘንድ ግድ ሆኗል። ለምን ብለን መጠየቃችን ለጉዳዩ መልስ መፈለጋችን አልቀረም። ብዙዎቹ በራስ መተማመናቸው ዝቅተኛ ነው ከዛም የተነሳ የነሱ አስተዋጾ አይደለም ያንተም የሌሎቻችን ጥረት ለውጥ ያመጣል ብለው አያስቡም። የሰው ልጆች ግማሾቹ ባርያ ሌሎች ደግሞ ጌቶች ተብለው ይኖሩ በነበረ ጌዜ ባርነት አይገባንም በሰውነታችን እኩል ነን ብለው በቻሉት ሲታገሉ የነበሩና ባርነት እጣ ፋንታችን ነው ከባርነት ነጻ መውጣት መቼም አንችልም የሚያምጹትንም አመጻችሁ የበለጠ ስቃይ ነው ትርፉ ይሉ የነበሩት አይነት ማለት ነው። በርግጥ አሁን ላይ ሆነን ስናየው እንደዚህ የሚያስቡ ነበሩ ብሎ ለማሰብ ቢከብድም።

ሌላው የነመለስ የግፍ ሰለባ ከሆኑት ጎን ከቆሙ ወይም የወያኔን የነመለስን ዘርፈ ብዙ ጥፋት ላይ ከተስማሙ። ንጹሀንን፤ መግደል፤ ማሰር፤ ማንገላታት ትክክል አይደለም አገር የመሸጥ መብት እነመለስ የላቸውም ካሉ የሚቀጥለው ጉዳዩን በአደባባይ መቃወም መታገል ትግሉን በእውቀትም በገንዘብም ማገዝ ነው። ይህቺን ደግሞ አይፈልጓትም የዛ አይነት አስተያየቶች የትግሉ አካል ላለመሆን ሰበብ መሆኑ ነው። ከጀርባ ያለው የተደበቀው ምክንያት ሌላ ነው። የተለያየ ምክንያት ሊሆን ይችላል ምክንያቱ ግን ሲመረመር ንጽት ያለች ፍረሀት ስላለችባቸው ነው። አገርቤት እንዳሌሄድ ፍረሀት ነው፤ የሰራሁትን ቤት ፍረሀት ነው። ቤተስቦቼ ፍረሀት ነው። ምንም በሉት ሁሉም ምክንያት ውስጥ ፍረሀት አለ። ተጎጂውን ተበዳዩን እንዳጠቁ አጥፊውን አገር ሻጩን ደፍረው ሳይቃወሙ ምክንያታቸውም ፍረሀታቸውን የሚያወጣ ስለሆነ የተደበቀ ምክንያታቸውን አውጥተው ሳይናገሩ እንደለዘቡ ተጎጂው ላይ ሰበብ ፈልገው እንዳንኳሰሱ ይቀጥላሉ። "አዎ ቴዲ አገር ቤት ማን ተመለስ አለው፤ ብርቱካን አርፋ ለምን ልጇን አታሳድግም።"

እነዚህን ሰዎች በነገሮች ላይ ሀሳብ ሲሰጡ መስማት ከማናደድም አልፎ እራስ ነው የሚያሳምመው። ዛሬ የምንታገልባቸው መለስ ሰራቸው የምንላቸው ሀጥያቶች ነብስ ካወቅን ጀምሮ በልቦናችን ያሉ አስርቱ የአምላክ ህጎች ናቸው። መስረቅ መግደል እነመለስ እየፈጸሟቸው ያሉ የቀን ተቀን ድርጊቶች ናቸው። ሌሎችን እንደራስ አለመውደድ አንዴ ጋንቤላውን፤ አንዴ አማራውን፤ አንዴ ኦሮሞውን እየለያዩ መጨፍጨፍ ማሰር ማንገላታት። ታላላቆችን አለማክበር የሰባ አመት ሽማግሌ መደብደብ ማዋረድ ባሏን አስረው ሲወስዱ ታስቦበት ሳይሆን ከውስጥ በስሜት የሚወጣ ጩህት ስላሰማች የአምሳ አራት አመት ሴት በጥይት ጭንቅላቷን መፈርከስ፤ መሾርመጥ። በእግዚአብሄር ሳይሆን በክላሽ ማምለክ። ሳያምኑ ደግሞ ፈርሀ እግዚአብሄር የለም። ታዲያ እንዚህን የእግዚአብሄር ህጎች ነፍስ ያወቀ ልብ ውስጥ ሁሉ አሉ፤ ስናድግ ከቤተሰብ ጀምሮ ከኖርንበት ህብረተሰብ ሁሉም ሀይማኖቶች ያስተማሩንን ናቸው፤ ውጪም ከወጣን በኋላ የምንኖርበት ማህበረሰብ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው። ስራ በቀያየርን ቁጥር የሰውን ልጅ በዘር በሀይማኖት በጾታ መለየት ማንጓጠጥ ወንጀል መሆኑንን ተምረን ገብቶናል ብለን አርባ ጊዜ የፈረምንበትን ጉዳይ ነው። ለእንጀራችን አክብረን የምንኖረውን እንዴት ህግ ነው። ታዲያ ምኑን ነው አንዳችን ለአንዳችን የምናስተምረው። ስንቶቻችን ነን በአጋጠሙን ቁጥር ተከራክረን ፖለቲካል ትንታኔ ሰተን የማያውቁትን አዲስ ነገርን ልናሳውቃቸውና ልናሳምናቸው የቻልነው።

"እነመለስ እንደሚገሉ እያወቁ ማን አምጹ አላቸው ፤ የወያኔን ባህሪ እያወቀች ብርቱካን ለምን በድርድር ተፈታሁ አለች፤ ቴዲ አብዝቶት ነበር ወይም ለምን አገር ቤት ተመለሰ" ሲሉኝ መከራከርም ፖለቲካል ትንታኔም መስጠት አሁን አሁን አቁሜያለው ንግግሩን ወደ ሀሳብ ሰጪው አዞርና ትፈራለህ አይደል ብዬ ደረቅ ጥያቄ ነው የማቀርበው ወይም የቴዲና ያንተ የሞራል ደረጃ ወይም ጥሩና መጥፎን የመለየት ችሎታችሁ በጣም ልዩነት አለው ብዬ ሀሳብ እሰጣለው። የማውቅው ሰው ከሆነ በፊት የነገረኝን የሆነ ነገር እፈልግና በደልን መቻል እንደምትችል ይታይብሀል ለዛ እኮ ነው በቀደም አለቃህ በቀደም የነገርከኝን ነገር ያደረገብህ የመሰለ ነገር እለዋለው ። ከዛ በኋላ ፍሪ አለመሆኑ ሊያሳይ ወይ ጠንካራ ሞራል ያለው መጥፎና ጥሩውን መለየት እንደሚችል ለማስረዳት አለቃውም ላይ ሌላ ምክንያት ለማቅረብ ሲጥር እኔም ያመጀመርያውን ሀሳቤን አጠንክሬ ስከራከር ስደበር እቆያለው። ጥቅሙ ግን ምን እንደሆነ አላውቅም እንደድሮው አልናደድም ሀሳብ ሰጪው አቶ ተጎጂውን ተበዳዩ ላይ አንበሳው ግን ይናደዳል። ይህን አይነት ችግር ያለባችሁ ሞክሯት ትሰራለች። እግረመንገዳቸውን ስለራሳቸው እንዲያስቡ ሳትረዳም አልቀረችም ነገር አሳድረው በሚቀጥሉውም ቀን የሚያነሱ የሚያለዝቡ ገጥመውኛል፡፡

ይህ አህያውን ፈርቶ ዳውላው ላይ አንበሳ የሚሆኑ ሰዎች የተወሰኑ ናቸው። በጣም ጠንካራ አቋማቸው ትክክለኛ የሆኑ ደፋሮች በየቦታው በየቤቱ በብዛት ነው ያሉት። በአሁኑ ጌዜ በአግባቡ ማስተባበር አለመቻሉ እንጂ ትግሉ ከሚያስፈልገው በላይ ናቸው። ኢትዮጵያዊያን እያልኩ ስለገለጽኩ ብዙ መስለው እንዳይወሰዱብኝ። በተረፈ ግን ተበዳዩን ተጠቂውን የሚያጠቁ ፖለቲከኞቻችንም እየታገሉ እየመሰሉ እራሳቸውን ስለሚሸነግሉና ፖለቲካል ትንታኔ ሰተው ብዥታ ስለፈጠሩብን እንጂ ያው አህያውን ፈርቶ ዳውላው ላይ አንበሶች ናቸው። አንዴ ከምርጫው በኋላ

ታስረው ከነበሩ የቅንጅት አመራርና ምሁር እንዳስቀመጡት ብዙዎችም የዚህ ጉዳይ ሰለባ የሆኑ የሚጋሩት የሚመስለኝ “ወያኔ ያለጥፋታችን አስሮ ሲያስቃየን እንኳ አሁን እየተጎዳን ያለውን ያህል አልተጎዳንም ዛሬ ከኛ አልፎ ይህ ጉዳይ ቤተሰቦቻችንንም እየጎዳ ነው ትልቅ የስለንቦና ችግር እየፈጠረብን ነው“ እስኪሉ ነው ጥቃት እየተፈጸመ ያለው። ዛሬ የብርቱካን ልጅ ትለቅ ብትሆን ምን ይሰማት ነበር ምን አይነት የስለንቦና ችግር ነበር የሚገጥማት። እነዚህ የተደራጁ ፖለቲከኞች ወያኔን እየታገሉ ጎን ለጎን የሚያደርጉት ጉዳይ እንኳ አይደለም ተጎጂውን ማጥቃት የሙሉቀን ስራቸው ሆኗል።

ለምን ብላችሁ ምክንያታቻውን የፈረደበት ፖለቲካል ትንታኔያቸውን ለመረዳት ስትሞክሩ፤ ስትመረመሩ የመጨረሻ ውጤቱ ፍረሀታቸውና በይበልጥም ግን ወያኔን ማሸነፍ አንችልም የምናደረገው ነገር ለውጥ ያመጣል ብሎ ካለማመን ተስፋ ከመቁረጥ የመጣቸ ነው።

ዳዊት ነኝ ከዳኮታ